በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ.210727

ቀን፡-28/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ገቢዎች ቢሮ - ዐቃቤ ሕግ ማዘንጊያ ደምሴ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አዕምሮ ዘሪሁን

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው ተጠሪ በባሕር ዳር ከተማ ገቢዎች መምሪያ የታክስ ኦዲትና የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት አስተባባሪነት ከነበሩበት ኃላፊነት ተነስተው ከደረጃ 9 ወደ ደረጃ 8 ዝቅ ብለው በሽያጭ መመዝገቢያ ኤክስፐርት ሆነው እንዲሰሩ በመመደባቸው ቅሬታ አቅርበው ተቀባይት በማጣቱ ለአማራ ክልል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአስተዳደር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ጥፋት ሳይኖረብኝና የዲሲፕሊን ክስ ሳይቀርበብኝ ከሥራ መደቡ መነሳቴ ሆነ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ መደረጌ አግባብ አይደለም የሚል ሲሆን አመልካች ባቀረበው መልስ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 9(4) መሠረት ማንኛውም የሥራ ሂደት አስተባባሪ በአሳማኝ ምክንያት ከኃላፊነት ሲነሳ ከያዘው መደብ ዝቅ ብሎ እንደሚመደብ ስለሚገልጽ በዚህ አግባብ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተከናወነ ነው ብሏል፡፡ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ከደረጃ 9 ወደ ደረጃ 8 ዝቅ ብለው እንዲሰሩና ደመወዛቸው እንዲቀነስ የተደረገው ጥፋት ያለባቸው ስለመሆኑ ወይም የሥነ-ምግባር ጥሰት መፈጸማቸው የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦ ሳይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ መሆኑ ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን የሚጥስ ነው በማለት የተጠሪ መሥሪያ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የአመልካችን የይግባኝና የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዘዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪ የዕውቀትና ክህሎት ክፍተት ያለባቸው እና የሥነ-ምግባር ጥሰት የፈጸሙ በመሆኑ ከሥራ መደባቸው መነሳታቸው ተገቢ ነው፡፡ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 9(4) መሠረት የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ የሥራ ሂደት ባለቤቶችን ያለዲሲፕሊን ክስ ሂደት ምደባ ማስተካከል ይችላል፡፡ ቅሬታ ቀርቦ አመልካች በሚሰጠው ውሳኔ ላይ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የማየት ሥልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ፍሬ ነገሩን አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የሠጡት መልስ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት በሕግ ሥልጣን ያለው አካል ነው፡፡ አመልካች ያለዲሲፕሊን ክስ ከሥራ መደብና ከደረጃ የማንሳት ሥልጣን በሕግ አልተሰጠውም፤ ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙን ክርክር፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ በባሕር ዳር ከተማ ገቢዎች መምሪያ የታክስ ኦዲትና የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት አስተባባሪነት ከነበሩበት ኃላፊነት ተነስተው ከደረጃ 9 ወደ ደረጀ 8 ዝቅ ብለው በሽያጭ መመዝገቢያ ኤክስፐርት ሆነው እንዲሰሩ በመመደባቸው ጥፋት ሳይኖርብኝና የዲሲፕሊን ክስ ሳይቀርብብኝ ከሥራ መደቡ መነሳቴ ሆነ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ መደረጌ አግባብ አይደለም የሚል ክርክር አቅርበው በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከደረጃ 9 ወደ ደረጃ 8 ዝቅ ብለው እንዲሰሩና ደመወዛቸው እንዲቀነስ የተደረገው ጥፋት ያለባቸው ስለመሆኑ ወይም የሥነ-ምግባር ጥሰት መፈጸማቸው የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦ ሳይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ መሆኑ ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን የሚጥስ ነው በማለት የተጠሪ መሥሪያ ቤት ውሳኔን በመሻራቸው የቀረበ የሠበር አቤቱታ ነው፡፡

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም በሚል ጭብጥ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘ ሲሆን በአማራ ክልል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 4 ላይ እንደተመለከተው የሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን በመንግስት መሥሪያ ቤትና በመንግስት ሠራተኞች ላይ ነው፡፡ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም ከሥራና ከሠራተኞች ጋር በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ጉዳዩን የመመልከት ሥልጣን በአዋጁ ተሰጥቶታል፡፡ በመርሕ ደረጃ ማንኛውም የክልሉ የመንግስተ ሠራተኛ የሚተዳደረው በዚሁ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ሕግ አውጪው ሲፈቅድና በተለየ ሕግ ሲደነገግ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞቻቸውን በተለየ ሕግ ሊያስተዳድሩ ይችላሉ፡፡ የአማራ ክልል የገቢዎች ባለስልጣን ተግባራትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 14 እና 8(1) መሠረት መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞቹን በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት እንደሚያስተዳድር ተመልክቷል፡፡ ይህን ተከትሎም ደንብ ቁጥር 79/2003 የተደነገገ ሲሆን ሠራተኞቹን የሚተዳደሩበትን ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዟል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን የሚያስተዳድረው በተለየ ሕግ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በደንቡ አንቀጽ 44(1) ላይ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ተፈጻሚነቱ በደንቡ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በደንብ ቁጥር 79/2003 ላይ የገቢዎች ባለስልጣን ሠራተኞች የሥራ ክርክርን የሚመለከት የዳኝነት ሥልጣን ያለው አካል አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም በደንቡ የሥራ ክርክርን የሚመለከት አካል ማን እንደሆነ ያልተሸፈነ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 253/2010 መሠረት የተቋቋመው የአስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 80 ከተሰጠው ሥልጣን መካከል የደመወዝ መቀነስ አንዱ በመሆኑ ተጠሪ ከሥራ ደረጃና መደብ ዝቅ ተደርገው የተቀነሰው ደመወዛቸው ላይ ይግባኝ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አቅርበው መታየቱ ተገቢ በመሆኑ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በሰበር አቤቱታው ተጠሪ የዕውቀትና ክህሎት ክፍተት ያለባቸው እና የሥነ-ምግባር ጥሰት የፈጸሙ በመሆኑ ከሥራ መደባቸው መነሳታቸው ተገቢ ነው፡፡ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 9(4) መሠረት የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ የሥራ ሂደት ባለቤቶችን ያለዲሲፕሊን ክስ ሂደት ምደባ ማስተካከል ይችላል በሚል ያቀረበው ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሀ) እና (ሸ) እንዲሁም አንቀጽ 10(1)(ሐ) እና (መ) መሠረት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን ባለመሆኑ፣ ግልጽ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔንና የሕግ ትርጉምን ያልተቃረነ ስለሆነና ጉዳዩም ከተከራካሪዎች ባለፈ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ቀርቦ የሚመረመር ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 105612 ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ/ም፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 55215 ግንቦት 12 ቀን 2015 ዓ/ም እና የአማራ ክልል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10251/2013 ሚያዚያ 18 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም